# ሀቀኛ ድርጅቶችን ያገለለ ሕብረት እፍረት

ንጋቱ ከበደ

ሰሞኑን በየፓልቶኮች በሚገባ ጆሮአችንንየሳበ ውይይት የተደረገበት ጉዳይ ነበር፡፡ የጋራ ግንባር፣ ሕብረት፣ ቅንጅት፣ጥምር ወዘተ፡፡ እንደሚታወጅ እየተጠባበቅን ነበር፡፡ ትግሉ ባለመሰባሰቡ ሰብሳቢ መጣሁ ሲል የማይሰማ ጆሮ መኖሩ ለምን ይጠበቃል? እንዲያውም ሲሆንማ በሚሊዮን ወጥተን የደስደሱ ተካፋይ መሆናችንን በሰላማዊ ሰልፍ መግለጽ ይጠበቅብናል፡ አዋጅ አሰሚዎቹም ይህን ካላደረግን ይቀየሙን የለ? ወሬውን ሰማሁና ሰምቼው በማላውቀው ድህረ-ገጽ ላይ ይህን አስመልክቶ መግለጫ እንደወጣ አየሁና አነበብኩት ጉጉት በማይሉት ጉጉት፡፡ አንዴ አይይደለም አምስቴ፡፡ እንዴት አንዴ አንብቤ ሳይገባኝ አምስቴ አስነበበኝ? ደግሞ በዝዛ ቋንቋዬ፡፡

ሳይከካ አልተቦካምና ከወሬት በፊት የዛሬው መግልጫ እንደሚወጣ በቀኑ እርግጠኛ ሆነን መናገር ባንችልም መሆኑ እንደማይቀር የታወቀ ነበር፡፡ የምጠብቀው በመደምደሚይ በቁጥር 4ያስቀመጡት “. . . አገራዊ ጥርሪ እናቀርባለን” የሚለው የመግልጫው ፈታውራሪ ሆኖ ይቀርባል የሚል ያላጠራጠር ግምት ነበረኝ፡፡ ቀደመም አልቀደም ፀገር መሰንጠቅ አይሆንብህም የሚለኝ አይጠፋም፡፡ እኔም ዋናው ቁም ነገር መልዕክቱ ነው ብዬ ለማሰብ ሞክሬ ነበር ግን አልዋጥ አለኝ፡ ጽሁፉ ይሆን ወይም ቡድኖቹ ፈራ-ተባ የሚል የፈዘዘ ወኔ የሚታይባቸው ይመስላል፡፡ ዋነኛው መልዕክታቸው በዋነኛነቱ መወጣት መቻል ነበረበት፡፡

ሌላው ያስገረመኝ ነገር ደግሞ የስብስቡ አይነት ነው፡፡ አራት እንጃ ቡድኖች ማለትም

- ኢህአፓ - ዲሞክራቲክ
- የግንቦት ሰባት ንቅናቂ
- የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት
- የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ
- የተቀሩትን ሶስቶቹን ስለማላውቃቸው የምለውም ነገር የለኝም፡፡

የአንድነት ለፍትህና ዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማኅበራት ካናዳና አሜሪካ የተባሉት የሚመስለኝ በኢትዮጵያ ያለው የወይዘሮ ብርቱካን ፓርቲ ደጋፊ ይመስሉኛል ካልተሳሳትኩ፡፡ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ፓርቲውን ወክለው ያቋም መግለጫ መስጠት መቻል አለመቻላቸውን ባላውቅም ቀልበ እንደሚነግረኝ ስህተት ይመስለኛል፡፡ የሞተውስ ሕብረት እንዴት ነብስ ዘርቶ አለሁ ለማለት በቃ? የኢሕአፓው እንጃ ራሱ ያጸደቀው መግለጫ ሰለባ መሆኑን ምናልባት ይህን ጽሁፍ ካነበበ በኋላ ይባንን ይሆናል፡፡ የመግለጫው አምስተኛ አንቀጽ ሲጀምር “<u>አብዮታዊ-ዲሞክራሲ</u>” የሚለውን የወያኔ ፕሮግራም ለመተቸት መግለጫው ሞክሮ “. . .ግራ የተጋባ ፕሮግራም ..” ይለዋል፡፡ አንጃውም ያሚዝለት መስለ😐 አብዮታዊ ዲሞክራሲ ነው እኮ መጠሪያው፡፡አንድ ግን ሊመሰገኑበት የሚገባ ነገር ቢኖር የነ ጸጋዬ ደብተራውና የማነ አብን ስም መጥቀሳቸው ነው፡፡ በተለይም ደብተራው የኢሕአፓ በማለታቸው ረክቻለሁ፡፡ ደብተራው የኢሕአፓ- ዲ አለማለታቸው!!! አባባሌ ቀልድና የማይረባ ሊመስላቸው ይችል ይሆናል፡ ግን መልዕክት አለው፡፡

ጥሪው መደረጉስ መልካ፡ ፍጥነቱም የተጠበቀ ነው፡ የተገንጣይ ድርጅቶችም አሉባችሁ ሲባሉ ነበር፡፡ የሕዝቡን ቁጣ ሰምታችሁ ከሆነ ያላስገባችኋቸው ይህም ድንቅ ነው፡ በኋላ ግን ብቅ እንዳታደርጓቸው፡፡

ባጭሩ መግለጫውን ጠለቅ ብሎ ላነበበው ብዙ ሊባል የሚያስችል ነግሮችይንፀባረቁበታል፡፡ ለኔ እንዳልጣመኝ ሁሉ ለሃቀኛ ድርጅቶችና ግለሰቦችም እንደማይጥም አልጠራጠርም፡፡ በጋራ መታገልን ማንም አይቃወምም፡፡ ግን የጋራ ግንባሩ መደራጀት ያለበት በወገቡሰባራ፣አድርባይ፣ ባንዳና እንጃ ጥርቅሞች ሳይሆን ከሕዝቡ ጋር በቆሙ ድርጅቶች ስለመሆኑ ያለመጠራጠር የማምነው ሃቅነው፡፡ ይህ ግንባር “ሰው ጥራ ቢሉት ራሱ መጣ” አይነት እንዳይሆን፡፡